ኔትወርክ ኦፍ ኔትወርክስ ኦፍ ኤች.አይ.ቪ ፖዘቲቭስ ኢን ኢትዮጵያ-ኔፕ ፕላስ
NETWORK OF NETWORKS OF HIV POSITIVES IN ETHIOPIA-NEP+

CENTERS FOR DISEASE CONTROL AND PREVENTION

## አሁንም ትኩረት ለኤች.አይ.ቪ መከላከል

# ጥምረት / TIMRET

ቅጽ 6 ቁጥር 1 ጥር 2012

Volume 6 Issue 1 Feb. 2020

## የዓለም የኤድስ ቀን በአፋር ክልል በድምቀት ተከበረ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ33ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ32ኛ ጊዜ የዓለም ኤድስ ቀን በአፋር ክልል ሰመራ ከተማ ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም. የኢፌድሪ ፕሬዚዳንት ክብርት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ በተገኙበት በድምቀት ተከብሮ ውሏል፡፡





በዓሉ በክልሉ የብሄር ብሄረሰቦች አዳራሽ ሲከበር የኢፌድሪ ፕሬዚሳንት ክብርት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ ፣ የክልሉ ርዕሰመስተዳድር የተከበሩ አቶ አወል አርባ፣ የፌደራል ኤች.አይ.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ጽጌሬዳ ክፍሌ ፣ የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ፣ የኔትወርክ ኦፍ ኔትወርክስ ኦፍ ኤች.አይ.ቪ ፖዘቲብስ ኢን ኢትዮጵያ (ኔፕ ፕላስ) ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮንን አለሙ፣ የአሜሪካ ኤምባሲ ተወካይ ሚስተር ዴቪድ ሬንዝ በበዓሉ ላይ ተገኝተው በስፍራው ለተገኙ የክልሉ ባለስልጣናትና ለሰመራና ለአካባቢዋ ከተሞች ነዋሪዎች ንግግር አድርገዋል፡፡

በተለይ የኢፌድሪ ፕሬዚዳንት ክብርት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ ባደረጉት ንግግር ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቀናጀ የማህበረሰብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡ ፕረዚዳንቷ አያይዘውም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በተደራጀ መልኩ በኤድስ ላይ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኔፕ ፕላስ ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮንን አለሙ በበኩላቸው በሀገሪቱ ባለፉት አመታት በኤድስ ላይ የተገኘውን መልካም ውጤት በማስታወስ ለዚህ ደረጃ ያበቁትን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አመስግነዋል፡፡



ዋና ዳይሬክተሬ አያይዘውም በቅርቡ ባለፉት ጥቂት አመታት በአንዳንድ የሀገሪቱ ከተሞች ዳግም ኣዳዲስ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር መጨመሩን በማንሳት ለዚህም እንደምክንያት የሆኑትን ነጥቦች ዘርዝረዋል፡፡ እንደዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ የአመራር ቁርጠኝነት አናሳ መሆን፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አናሳ መሆን፣ ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸው ማህበራት የሚደረገው ድጋፍ እና ክትትል አናሳ መሆን አሁን እንደ አዲስ እያገረሸ ለመጣው የኤድስ ወረርሽኝ ከመንስኤዎቹ መካከል ዋንኛዎቹ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሲ ምክትል ዲፕሎማቲክ ልዑክ መሪ ዴቪድ ሬንዝ የ2019 የፔፕፋር መርህ የኤድስ ወረርሽኝን ማቆም፤ ማህበረሰብ ለማህበረስብ የሚል እንደሆነ በመጠቆም መርሁ ከማህበረሰብ ጋር ጠንካራ የሆነ ግንኙነት በመመስረት ሰብአዊ ተኮር፣ ከአድሎ ነጻ የሆነ ኤች.አይ.ቪ ህክምናና እንክብካቤ አገልግሎት መስጠት አስፈላጊነት በተመለከተ ያገኘንውን ትምህርት አመላካች ነው ብለዋል፡፡



በዕለቱ የአፋር ህዝቦችን ባህል የሚያንጸባርቁ የሙዚቃና የስፖርት ትርዒቶች ቀርበው በዓሉ ተጠናቋል፡፡

ከበኣሉ ማጠናቀቂያ ስነስርዓት በኋላ የኢፌድሪ ፕሬዚዳንት ክብርት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ ሰመራ ከተማ በአጭር ርቀት ላይ ወደምትገኘው የዱብቲ ከተማ በማምራት ሁለት የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው የኒገኝባቸው ማህበራትንና የዱብቲ ሆስፒታልን ጎብኝተዋል፡፡ በጉብኝቱ ወቅትም ከማህበራቱና ከሆስፒታሉ አስተዳደሮች ገለጻተደርጎላቸዋል፡፡



# ለሠራተኞች የፕሮግራም ማስጨበጫ ስልጠና ተሠጠ

የኔፕ ፕላስ ማኔጅመንት ለድርጅቱ ሰራተኛ አዲስ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን የሚያስተዋውቅ ስልጠና በአደማ ከተማ የሶስት ቀናት ስልጠና ሰጠ፡፡



የኔፕ ፕላስ ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮነንን አለሙ በስልጠናው መክፈቻ ላይ ባሰሙት ቃል ሁሉም የድርጅቱ ሰራተኞች በዩኤን ኤድስ፣የዓለም የምግብ ፕሮግራም እና በኢጥዮጵያ መንግስት እንደዚሁም ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች ተቋሞች ስራ ላይ የሚውሉ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ማወቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

ይህም የሚሆነው እንደ ዋነባ ዳይሬክተሩ ገለጻ ሁሉም የኔፕ ፕላስ ሰራተኛ የድርጅቱ አምባሳደር በመሆኑ በሚያገኛቸው አጋጣሚ ሁሉ በአካባቢው ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ድርጅቱና ድርጅቱ ስለሚያከናውናቸው በጎ ተግባራት በበቂ ሁኔታና በራስ መተማመን ለመናግር እኒዲችል ነው፡፡ ለእንዲህ አይነት ተግባር ደግሞ ይህን የመሰለ ስልጠና ወሳኝ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ አስምረውበታል፡፡



አቶ መኮንን አለሙ
የኔፕ ፕላስዋና ዳይሬክተር

በተመሳሳይ የድርጅቱ የፕሮግራም መምሪያ ኃላፊ አቶ ድንቄ ወርቁ በፍቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በቤተሰብ አባላት መካከል ስለሚደረግ የኤቭ.አይ.ቪ ምርመራ ፕሮግራም ማብራሪ ሰጥተዋል። በዚህ ፕሮግራም መሰረት አስቀድሞ አንድ የቤተሰቡ አባል ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደሙ ከተገኘ በኋላ ቀሪውን የቤተሰብ አባላት በፍቃደኝነት እንዲመረመሩ ይደረጋል። ይህም የቤተሰብ አባላቱ ውጤታቸውን አውቀው መውሰድ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ እንደሚያስችላቸው ኃላፊው ተናግረዋል።

ይህ ተግባርም በሶስት ክፍሎች የተከፈሉ ሲሆን ፋሚሊ ኔትወርክ፣ የአጋር ጥምረት አገልግሎት እና ማህበራዊ ጥምረት አገለግሎት ናቸው። አዳዲስ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር መቀነስ፣ በቫይረሱ ለተያዙ ሰዎች የምክር አገለግሎት መስጠት መቻል የዚህ ፕሮግራም አላማዎች እንደሆነም ከቀረበው ጥናት ለመረዳት ተችሏል ።

አቶ ንጉሴ ገብሬ በድርጅቱ የፕሮግራም ሰራተኛ በበኩላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የጸረ-የኤች.አይ.ቪ ህክምናና ስለ ሶስተኛ ደረጃ ህክምና በተመለከተ እንደዚሁ ለሰራተኛው ትምህርት ሰጥተዋል።

አቶ ንጉሴ በገለጻቸው ላይ እያይዘውም አሁን ላይ ህጻናት ተገቢውን የጸረ- ኤች.አይ.ቪ ህክምና እያገኙ እንዳልሆነ አመልክተዋል።




አቶ ድንቄ ወርቁ
የኔፕ ፕላስ ፕሮግራም መምሪያ ኃላፊ

በአሁኑ ወቅት ወደ ሁለተኛ ደረጃ የጸረ-ኤች.አይ.ቪ ህክምና የሚገቡ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑንም ከቀረበው ገለጻ ለመረዳት ተችሏል።



አቶ ንጉሴ ገብሬ
የኔፕ ፕላስ ፕሮግራም ባለሙያ

ከሁለቱ አሰልጣኞች ቀደም ብሎ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ መኮንን አለሙ በስራ ቦታ ስለሚፈጠር መጨናነቅና ይህን መጨናነቅ አስወግዶ ራስን ለስራ ዝግጁ ስለሚደረግበት ሁኔታ ለሰራተኛው ትምህርት ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል የኔፕ ፕላስ ሰራተኛ ሶሻል ኮሚቴ ሊቀመንበር አቶ አስፋው አሸናፊ በበኩላቸው ስልጠናውን አስመልክተው በሰጡት አስተያየት እንዲህ ያለው ስልጠና ለሰራተኛው አስፈላጊ መሆኑን ተናግረው ሰራተኛው የድርጅቱን ዓለማ ለማሳካት ያልተቆጠበ አስተዋጽኦ እንዲያደርግም ያስችለዋል ብለዋል ።



አቶ አስፋው አሸናፊ
የኔፕ ፐላስ ሰራተኞች ሶሻል ኮሚቴ ሊቀመንበር

# ከሀይማናት ተቋማት ጋር ውይይት ተካሄደ

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዓለማችን ብሎም በሀገራችን ከተከሰተ ወዲህ በርካቶች በወረርሽኙ ተይዘው ህይወታቸው ቢያልፍም እንደዚሁ ብዙዎች በጽናት በመቋቋም የጸረ-ኤች.አይ. ቪ ህክምና አገልግሎት እስከተጀመረበት ጊዜ በመድረስ በህክምናው ተጠቃሚ ሆነው ጤናቸው ጠብቀው እስካሁን ድረስ ሲኖሩ ስተዋላል፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ አመታት ወዲህ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖች ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በሚከተሉት የሀይማኖት ሳቢያ መድሀኒታቸውን በማቋረጥ ለተለያዩ በሽታዎችና በመጋለጥ እስከመሞት እየደረሱ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ኔትወርክ ኦፍ ኔትወርክስ ኦፍ ኤች.አይ.ቪ ፖዘቲቭስ ኢን ኢትዮጵያ (ኔፕ ፐላስ) ከፕሮጀክት ሆፕ ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከሚገኙ የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት ተወካዮች ጋር አንድ ቀን ስብሰባ በአዳማ ከተማ አካሂዷል፡፡

ስብሰባውን የሙስሊም እና የኦርቶዶክስ አባቶች በቡራኬ ስጀመሩት ሲሆን የስብሰባውን አላማ በተመለከተ የኔፕ ፐላስ የፕሮግራም መምሪያ ኃላፊ አቶ ድንቄ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በኃላፊው ማብራሪያ መሰረት የውይይቱ ዋና ዓላማ የሁሉም ሀይማኖት ተከታዮች እና ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ አንዳንድ ወገኖች ሀይማኖትን ሰበብ በማድረግ የጸ-ኤች.አይ.ቪ ህክምናቸውን እያቋረጡ ስለሚገኙ እዚህ ላይ ለመምከርና እነዚህን ወገኖች ወደ ህክምናው መመለስ ስለሚቻልባቸው መንገዶች የመፍትሄ ሀሳብ ለማፈላለግ ነው፡፡



በማስከተልም በኔፕ ፐላስ በም/ዋና ስራ አስኪያጅ ማዕረግ የሀብት ማፈላለግ መምሪያ ኃላፊ አቶ ባይሳ ተሰብሳቢዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ካደረጉ በኃላ ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጥናት አቅርበዋል፡፡

ጥናቱ ካካተታቸው ሀሳቦች መካከልም ለዘርፈ ብዙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ የኃይማኖት ተቋማት ምላሽ፣ ከሀይማኖት ተቋማት ጋር መስራት ሚያስገኘው ጠቀሜታ፣ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖች የጸረ-ኤች.አይ.ቪ ህክምናቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ለማድረግ የሚኖራቸው ሚና እና ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝባቸው ወገኖች ከሀይማኖት ተቋማት የሚጠብቁት ምላሽ የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡



አቶ ባይሳ ጫላ
ምክትል ስራ አስኪያጅና የሀብት ማፈላለግ መምሪያ ኃላፊ

የተቋማት ተወካዮቹ በቀረቡት ሀሳብ ላይ ተወያይተው ጥቂት የሀይማኖት መሪዎች ከሀይማኖቱ አስተምሮት ደምብ በማፈንገጥ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸውን አንዳንድ ወገኖች ከህመማችሁ በፀበል፣ በፀሎት እና በመሳሰሉት የሀይማኖት ስርዓቶች ተፈውሳችኋል ከዚህ በኋላ የጸረ-ኤች.አይ.ቪ ህክምና አያስፈልጋችሁም በማለት ግለሰቦቹን ለከፋ ችግር እንደሚዳርጓቸው በመጥቀስ ለዚህ መፍትሄ መፈለግ እንደሚያሻ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

በዚህም በቀጣይ የተለያዩ ስራዎች ለመስራት ቁርጠኝነታቸውን አሳይተዋል፡፡ የሀይማኖት ተቋማት ተወካዮቹ በቀጣይ ለመተግበር ቃል ከገቡት ስራዎች መካከል ለከፍተኛ የሀይማኖት ተቋማት የስራ ኃላፊዎችና የሀይማኖት አባቶች ወቅታዊ የኤች.አይ.ቪ ሁኔታን ማሳወቅ፣ ለሀይማኖት ተከታዮቻቸው ስለ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ማስገንዘብ በተለይም ቫይረሱ በደማቸው ለሚገኝባቸው ወገኖች ህክምናቸው በአግባቡ እንዲከታተሉ ማስተማርና ከሀይማኖት ጋር ምንም አይነት ግጭት እንደሌለው ማሳወቅ፣ የሀይማኖት አባቶች ሀይማኖቱ የማይፈቅደውን አሳሳች ትምህርት ለምዕምናን በተለይም ቫይረሱ በደማቸው ላለባቸው ወገኖች እንዳያስተምሩ በተቋም ደረጃ መቆጣጠር የሚያስችል አሰራር መተግበር የሚሉ ይገኙባቸዋል፡፡

በዕለቱ በሌላ በኩል ተመሳሳይ ውይይት ከአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ አመራር ተወካዮች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡

## የበጎ አድራጎት ሚና

በናይጀሪያ አንድ በተካሄደ ጥናት እንደተመለከተው ብዙ ጊዜ የበጎ አድራጎት ማህበራት ሚና ተብሎ የሚገመተው በዜጎችና በመንግስት መካከል የኮምኒኬሽን/ተግባቦት ስራን ማመቻቸት ነው ፡፡ ይሁን እንጂ የበጎ አድራጎት ማህበራት ውጤታማነት መንግስት ለክቶ በሚሰጣቸው የመጫወቻ ሜዳና ከአጋር ድርጅቶች በሚመደበው የገንዘብ ድጋፍ እነደዚሁም በራሳቸው ባላቸው የውስጥ አቅም ይወሰናል፡፡

እዚህ በኛም ሀገር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሚመክር ስብሰባ በአዳማ ከተማ በኔፕ ፕላስና በሲሲኤም አማካኝነት ተካሂዷል፡፡ በስብሰባው የተለያዩ ሀገር በቀል በጎ አድራጎት ማህበራትና የመንግስት ድርጅቶች ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡



በስብሰባው የመጀመሪያ እለትም የኔፕ ፕላስ ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮንን አለሙ የስብሰባውን አላማ አስመልክተው የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል፡፡ እንደ አቶ መኮንን ገለጻ የሳንባ፣ የወባ እና የኤች.አይ.ቪ በሽታዎች ዋንኛ የኢትዮጵያ ህዝብ የጤና ችግሮች ናቸው ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍም የበጎ አድራጎት ማህበራት ከመንግስት በተጨማሪ የማይተካ ሚና አላቸው ሲሉ አቶ መኮንን በመግቢያ ንግግራቸው ላይ ተናግረዋል፡፡ ቀደም ሲል እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ስብሰባዎቸወ መካሄዳቸውን ያስታወሱት አቶ መኮንን ይህን ከቀድሞዎቹ የሚለየው ስብሰባው የተዘጋጀው እንደቀድሞዎቹ በመንግስት አካላትና ፖሊሲ አውጭዎች አሳሳቢነት ሳይሆን በራሳቸው የበጎ አድራጎት መነሻ ሀሳብ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በስብሰባው መጀመሪያም ከፌደራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የመጡ ተወካይ የጥናት ጽሁፋቸውን አቅርበዋል፡፡ አቅራቢው ጽሁፋቸውን ያቀረቡት የወቅቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሁኔታና ዋንኛ ተግዳሮቶቹ እንዲሁም የመፍትሄ ሀሳቦች በሚል ነው፡፡ እንደጥናቱ አቅራቢ አሁን ባለው ተጨበጭ ሁኔታ በሀገሪቱ ዳግም የኤች.አይ.ቪ ወረርሽኝ እያገረሸ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያም አዳዲስ በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥርም በሀገሪቱ እየቀነሰ አይደለም፡፡ ቁጥሩን ለመቀነስ በሚካሄደው ጥረት ምንም ዐይነት ለውጥ ከማይካሄድባቸውም ወይም ለውጡ ዝግመተኛ ከሆኑ ሀገሮች መካከል ሀገሪቱ እንደምትመደብም በጥናቱ ተገልፆአል፡፡

ጥናቱ አቅራቢው ሌሎች በርካታ ችግሮችን ያነሱ ሲሆን እንደመፍትሄም ያነሱት የአመራሩና የበጎ

አድራጎት ማህበራት ሚና መጠናከርና ተገቢውን ትኩረት ማግኘት አለባቸው የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ጥናት በተመሳሳይ የቀረበው ከኔፕ ፕላስ በኩል ሲሆን አቅራቢውም የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ መኮንን አለሙ ናቸው፡፡

አቶ መኮንን ባቀረቡት ጽሁፍ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖች ኤድስ ወረርሽኙን በመከላከል ረገድ የነበራቸው እና ወደፊትም የሚኖራቸው ሚናና ተግዳሮቶች በተመለከተ በስፋት ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ኗለም ማኅበራት እነዚህን ተከትሎም የብሄራዊ ጥምረቱ የክልል ጥምረቶች በማስተባበር ሰፊ ስራ ሲሰራ እንደቆየ ዋና ዳይሬክተሩ በጽሁፋቸው አብራርተዋል፡፡ ሆኖም በተለይ በዚህ ወቀት ዓለም አቀፍ አጋር ድርጅቶች ድጋፍ መቀነስ ማህበራት ትኩረት እንዲያጡና ከዚህ አልፎም እስከመፍረስ መድረሳቸው እንደትልቅ ተግዳሮት በጽሁፉ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ሌላው ቫይረሱ በደማቸው በሚገኝ ወገኖች እየተስታለ ያለው ችግር የመድሀኒት ማቋረጥና የመድሀኒት መላመድ ነው፡፡ ይህም ችግር ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ወገኖችና ማህበራታቸው ትኩረት ካላገኘ ሊባባስ እንደሚችል በጽሁፉ ላይ ተጠቁሟል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው ጥናት ቮለንታሪ ሄልዝ ሰርቪስ ከተሰኘ ምግባረ ሰናይ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የሚሰራው በሳንባ በሽታ ላይ በመሆኑ ጥናቱም ያተኮረው በሳንባ በሦታ መከላከል ረገድ በጎ አድራጎት ማህበራት ያበረከቱት አስተዋጽኦና ያጋጠሙ ችግሮች የሚል ነበር፡፡

ጥናት አቅራቢው በተለይ በበጎ አድራጎት ማህበረሰብ የሚሰባሰቡ የማህበረሰብ ክፍሎች በሁሉም አይነት የጤና ችግር ሲሳተፉ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ያደርጋሉ ወይ በሚለው ሀሳብ ትኩረት አድርገው ሲያብራሩ ማህበረሰብ አካላት በጤና ችግር ላይ ሲሳተፉ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎስ ጋር መድረሱ ብቻ በራሱ ትርጉም ያለው ተሳትፎ አያሰኘውም ብለዋል፡፡ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግም ማህበረሰቡ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የክትትልና ምዘና ስራ ላይ ጭምር መሳተፍ ኖርባቸዋል፡፡

በስተመጨረሻም በቀረቡት ጽሁፎች ላይ ተሰብሳቢዎቹ አጠቃላይ ውይይት አድርገዋል፡፡ ተሰብሳቢዎቹ ከተወያዩባቸው ጉዳዮች መካከል አራት ዋና ዋና ሀሳቦች ማውጣት ተችሏል፡፡ እነሱም ማህበራት በሚሰሩባቸው የጤና ችግሮች ዙሪያ በፖሊሲ አውጭዎችና በማህበረሰብ ዘንድ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጋር በመቀራረብ የአድቮኬሲ ስራዎች መስራት፡፡ ሌላው የተነሳው ሀሳብ የሀገር ውሥጥ ሀብትን ማፈላለግና ማደራጀት የሚል ነው በተለይ በዚህ ረገድ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ በበርካታ ድርጅቶች ያልተነኩ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰቡ ገንዘብ በኤድስ ፈንድ በሚል ርዕስ ላመታት ተከማችቶ ስለሚገኝ ይህንን ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የህግ መሰረት እንዲቀመጥ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መስራት እንዳለባቸው ስምምነት ላይ ተደርሷ፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የነሳው ሀሳብ አጋርነትን ማጠናከር የሚል ነው፡፡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ካላሻሻሉና ካላጠናከሩ ያስቀመጡት ግብ ላይ ለመድረስ እነደሚቸገሩ በውይይቱ ወቅት የተነሳ ሀሳብ ነው፡፡

አራተኛው ሀሳብ በጎ አድራጎት ማህበራት ራሳቸውን መፈተሸና ክፍተታቸውን በተለይ በአቅም ማሳደግ፣ በሚሰሯቸው ስራላይ የሚታየውን የማስረጃ አደረጃጀት /ዶክመንቴሽነን/ ችግር መቅረፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ለዕቅድ እና በጀት ዝግጅት አስፈላጊ በመሆኑ እንደሆነ በውይይቱ ላይ ተነስቷል፡፡ በጎ አድራጎት ድርጅቶቹ የሚከተሉትን ሁለት አበይ ነጥቦች በመለየት በቀጣይ በነዚህ ሀሳብ ላይ ትኩረት ሰጥተው ለመስራት አቅጣጫ አስቀምጠዋል፡፡

1. በጎ አድራጎት ማህበራት በሀገር አቀፍም ሆነ በአካባቢ መዋቅር ላይ በፕሮግራም ቀረጻ ፣ አፈጻጸም. በምዘናና ክትትል ስራ ላይ በመሳተፍ ትርጉም ያለው ተሳት እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት

2. የሀገር ውስጥ ሀብትን ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ስልት መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ በተለይም ተከማችቶ የሚገኘውን የኤድስ ፈንድ ጥቅም ላይ ለማዋል በመንግስት በኩል የህግ መሰረት እንዲፈጠር መስራት የሚሉ የወደፊት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ስብሰባው ተጠናቋል፡፡

# 2019 World AIDS Day colorfully marked in Afar Region, Samara Town

2019 World AIDS Day colorfully marked in Afar regional Administration with the presence of FDRP Government Ethiopia President, Her Excellency Ambassador Sahlework Zewde. The day was commemorated in Ethiopia for the 32nd time while it is 33th at global level.

During the event that took place in the region's nation, nationalities hall, Her Excellency Amasador Sahlework Zewde, The regional administration Head His Excellency Ato Awel Arba, Director General of FHAPCO D/ro Tsigereda Kifle, FDRE Ministry of Health State Minister D/r Lidiya, Deputy Chief of Staff Embassy of United States Mr. David Renz and Executive Director of NEP+ Ato Mekonnen Alemu have forwarded a key note speech to the audience. Especially Her Excellency Ambassador Sahlework Zewde said in her speech that community engagement is vital in the fighting of HIV/AIDS. She also called the Afar Community and regional government for their coordinated effort towards the end of AIDS.



Her Excellency President Sahlewerk zewde



participants of the event partially

NEP+ Executive Director Ato Mekonnen Alemu on his behalf he expressed his gratitude for government and nongovernment organization as well as for all actors who were involved in the combating of HIV/AIDS in the last 20 and 25 years. He underlined that as a result of this coordinated movement Satisfactory result was recorded against AIDS.



Ato Mekonnen Alemu
Executive Director of NEP+

The Executive Director said also mentioned that currently in some part of the country new HIV infection rate is aggressively increased. This is happened due to low commitment of government leaderships, low stakeholder engagement and minimal support to PLHIV association.

Deputy Chief of Party Embassy of United States, Mr. David Renz was the other speaker of the event. He reminded the 2019 PEPFAR world AIDS DAY theme of Ending AIDS epidemic, Community for Community. According to the ambassador the theme indicates the lesson that we have learnt the importance of providing person-centered and free discrimination HIV/ AIDS treatment and care by establishing strong community relationship.



Mr. David Renz
Deputy Chief of Party of Embassy of the United States in Ethiopia

During the day Afar traditional music and sport were presented by the regional tradition music and sport clubs.

After the event, Her Excellency Ambassador Sahlework Zewde visited Dubty Hospital and two PLHIV associations located at Dubty town some kilometer far away from Samara town.



The President while paying visit at Dupty town, Afar region

## Management updates the staff

Network of Networks of HIV Positives in Ethiopia updated its staff about new HIV prevention and care service program in a three day training session.



NEP+ executive Director, Ato Mekonnen Alemu, said while he explained the objective of the training during his opening speech that all of the NEP+ employee as a NEP+ staff should be aware of every new HIV programs developed by UNAIDS, WFP and Government of Ethiopia and other concerned body.

He underlined that every employee is an ambassador of the organization and he/ she must able to orate with confidence and comprehensive information about NEP+ to his/ her surrounding societies. In order to exercise this, such kind of timely update training is crucial, Ato Mekonnen said.



Ato Mekonnen Alemu,
Executive Director of NEP+

Accordingly, Ato Diku Worku, program manager of NEP+ presented his update on Index Case Testing (ICT). Index case testing is conducting HIV test willingly on a certain family after indentifying a person with HIV virus in the family, Ato Dinku said. This process has three types of approaches, according to Ato Dinku.

According to him Family Matrix (FM), Partner Network service (PNS) and Social Network Service (SNS). Reducing new HIV infection and providing ART treatment and counseling service for HIV positives persons are some of the the goals and objectives of this approaches, learnt from the presentation.




Ato Dinku Worku
NEP+ Program Manager

Ato Nigusse Gebre, program Officer of NEP+, also presented about TLD (a first line antiretroviral (ARV) fixed-dose combination) and national third line ART implementation manual. In his presentation he revealed that HIV positives children are not getting proper types of ART drug. He also clarified that number of second line ART drug registries is increasing.



Ato Niguse Gebre
NEP+ Program Officer

Earlier to the two presentations Ato Mekonnen Alemu, Executive Director of NEP+ presented about office burn out management. In his presentation he briefly explained about how stree happened and how it affects our office work and he also give a clue how one avoid such stress.

Ato Asfaw Ashenafi, Head of NEP+ staff Social Committee said on his behalf that such kind of updating training for staff member is important as it enable the employee to forward its unreserved contribution towards the objectives of the organization.



Ato Asfaw Ashenafi
NEP Plus staff Social committee Head

# Dialogue takes place with Religious Representatives

Many died because of HIV/AIDS, and many of them also resist it till the introduction of ART treatment. The strongest continues to live by adhering ART treatment properly.

However among them who continue their life with strong ART adherence, some are giving up in a mistakenly structured thinking. Because of this some are facing sever health difficulties even to death.

Having this in mind, NEP+ has conducted a one day consultative meeting with religious institutions found in Addis Ababa City.



The meeting began with Muslim and Orthodocs religious fathers' pray. Following the pray Ato Dinku Worku expressed the objective of the consultative program. According to him the aim of the meeting is to discuss about the PLHIVs who terminate their treatment because of religious cases and also to find a solution how these people could resume their medication.

Ato Baysa Chala, deputy Executive Director of NEP+ presented his paper focusing on the epidemic of HIV/AIDS and religious institution responses, benefit of working together with these institutions, Religious institutions' role on bringing back PLHIVs to treatment and expected response from religious institutions against the epidemic.



Ato Baysa Chala
Deputy executive director and Head of Resource Mobilization department

The religious representatives accepts that there are few religious persons mistakenly tell PLHIVS as if they are cured from HIV/AIDS after having holy water and pray without further diagnosis. They also admitted that this practice led the PLHIVs to unnecessary health problem.

In order to curb the problem, the representatives showed their commitment. They vowed to aware the problem to senior religious leader. They also determined to educate the public specially the PLHIV to adhere their treatment strongly.

On the other side, a discussion was held with Addis Ababa city sub city leadership on a similar agenda.

## Roll of Civil Societies Organizations

A study in Nigeria on Civil Societies Organizations stated that the roll of these organizations is assumed to be institutions facilitating communication between the public and government. However, CSO advocacy is only as effective as the space allowed by government, the resources available from funders, and their own internal capacity.

Here in Ethiopia also a one day consultative meeting on a similar issue has been organized by NEP+ and CCM/E at Adama town. In this consultative meeting various local Civil Society Organizations and representative of government organizations took part.



Ato Mekonnen Alemu, NEP+ Executive Director, said in his opening speech that Malaria, HIV and Tb are the major health problem of the human being. CSOs have indispensable role in regard to curbing these health problem, Ato Mekonnen added.

However similar consultative meetings were conducted, all of them were initiated by government bodies, Ato Mekonnen reminded the participants, and this one is organized by the CSOs initiation.

The meeting began by Federal HIV/AIDS Prevention and Controlling Office /FHAPCO/ presentation. According to the presentation, currently new HIV infection rate once again is increasing. The effort that has been underway to control the new infection also does not brought effective result.

The presentation stated various related challenges and recommended, to curb the problem that the political leadership and CSOs partnership must be strengthened and also should get adequate attention.

Ato Mekonnen Alemu, Executive Director of NEP+, the second presenter, explained PLHIVs previous roll in regard to mitigating HIV pandemic and also the challenges that faced them. Accordingly, during the first phase of HIV pandemic, in Ethiopia, few PLHIV individuals, then PLHIV associations and networks have played significant roll against HIV/AIDS.

However, currently because of falling down of global fund towards HIV/AIDS make many PLHIV associations to be left aside. And this lead many of them to be shrink.

Termination of ART treatment was the other problem raised by the presenter. Unless this problem get timely solution, the situation might be worse.

Voluntary Health Service, VHS, finally presented CSOs roll and contribution on the prevention of TB disease.

According to the presentation, meaningful CSOs engagement means when CSOs take part in the community based monitoring and evaluation systems.

During the general discussion, participants identified four major points in order to enhance the roll of CSOs in the national engagement. Accordingly, CSOs should be engaged in advocacy tasks, CSOs must solicit internal resources, especially in HIV/AIDS sectors there is untouched cumulated AIDS fund among many government organization. In order to utilize this cumulated fund CSOs should knock the policy makers' door continuously.

The third issue raised by meeting attendants was the necessity of enhancing CSOs partnership among them. CSOs unless they strengthen their partnership each other, It will be tough to meet their objective.

The final and fourth points that got attention by the participants was identifying CSOs their own gap and filling it. Especially CSOs should work on their documentation, which could help for planning and budgeting purpose.

The CSOs finally put the following two major the way forward

1. Facilitate CSOs to have meaningful in engagement in the program development, program implementation and monitoring and Evaluation.
2. Develop advocacy strategy to utilize the untouched and cumulated AIDS fund and implement the influencing activities accordingly.

Tel.+251 11 6 59 18 18 / 19 19 / 12 12
P.Box : 780/1250
Email : aelwha @ ethionet.et
Web . www. nepplus.org